በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር 3.J/J47/10
Ref. No.
ቀን 03 ግንቦት 2010
Date

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
ለምስራቅ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
ለምዕራብ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
ለታክስ አስተዳደር ማጣጣምና የክልል ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
ለደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
**የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን**
ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ባለስልጣን
**አዲስ አበባ**
ለአዳማ ቅ/ጽ/ቤት
ለባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት
ለድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት
ለመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት
ለኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት
ለሐዋሳ ቅ/ጽ/ቤት
ለጅማ ቅ/ጽ/ቤት
**በያሉበት**

በወጪ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች ለሚያስፈልጋቸው የወጪ ድጋፍና ለዕውቀት ሽግግር የሚቀጥሯቸው የወጪ ባለሙያዎች በመቀጠር የሚያገኙት ገቢ በወጪ መጋራት ሥርዓት ከገቢ ግብር ነጻ ስለሚሆኑበት ሁኔታ በፌዴራል መንግስት የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2010 አንቀጽ 54/1/ሀ ድንጋጌን መሰረት በማድረግ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያወጣውን የአፈጻጸም መመሪያ 7 /ሰባት/ ገጽ ከነሽኚ ደብዳቤው አያይዘን የላክን መሆኑን እየገለጽን በመመሪያው መሰረት ተፈጻሚ እንዲደረግ እናሳስባለን::

ከሠላምታ ጋር

የኢኒሻሽት በጋሻው
[ገ]ቢር ውስጥ ታክስ አሠራርና
[ድጋ]ፍ ዳይሬክቶሬት ምክትል
ዳይሬክተር

**ግልባጭ**፡
- ለአገር ውስጥ ታክስ ዘርፍ
**የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን**

ለዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!

ስልክ ቁ / Tel. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ/ Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ. / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ- ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance and Economic Cooperation

ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
<u>አዲስ አበባ</u>

በወጪ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች ለሚያስፈልጋቸው የሙያ ድጋፍ ለእውቀት ሽግግር የሚቀጥሯቸው የውጭ ባለሙያዎች በመቀጠር የሚያገኙት ገቢ በወጪ መጋራት ሥርዓት ከገቢ ግብር ነፃ ስለሚሆንበት ሁኔታ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚያወጣው የአፈፃፀም መመሪያ እንደሚወሰን በፌዴራል መንግስት የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2010 አንቀጽ 54 (1)(ሀ) ላይ ተደንግጓል። በዚሁ መሠረት ይህንኑ የሚወስነው መመሪያ በመ/ቤታችን ተዘጋጅቷል።

ስለዚህ መመሪያውን ከዚህ ጋር አባሪ አድርገን መላካችንን እየገለጽን በመመሪያው መሠረት እንዲፈፀም እንዲደረግ እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

Ethiopian Revenues & Customs Authority
Records & Documentation No.2

ግልባጭ፣
ለፊሲካል ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት
ለታክስ ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት
ለሕዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት
<u>ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር</u>

# በኤክስፖርት ተኮር የስራ ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች ለሚያስፈልጋቸው የሙያ ድጋፍ ለሚቀጥሩዋቸው የውጭ አገር ባለሙያዎች የሚከፍሉትን ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም ከገቢ ግብር ነፃ ለማድረግ የወጣ

## መመሪያ ቁጥር 52/2010

## 1. አውጪው ባለሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌዴራል ገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2010 አንቀጽ 54(1)(ሀ) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በኤክስፖርት ተኮር የሥራ ዘርፍ የተሰማሩ/የሚሠማሩ ባለሀብቶች ለልዩ ልዩ ሥራዎች ከውጭ አገር ቀጥረው የሚያመጧቸውን የውጭ ባለሙያዎች ከገቢ ግብር ነፃ ለማድረግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 52/2010" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

3.1 "ባለሀብት" ማለት ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን በማምረት ወይም በማቀነባበር ሥራ ላይ የተሰማራ ወይም የሚሠማራ ሆኖ ምርቱን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ኤክስፖርት የሚያደርግ አምራች ነው፡፡

3.2 "የወጪ መጋራት ሥርዓት" ማለት ባለሀብቶች ለሚያስፈልጋቸው የሙያ ድጋፍ ለሚቀጥሩዋቸው የውጭ አገር ባለሙያዎች የሚከፍሉት ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም ከገቢ ግብር ነፃ የሚደረግበት ሥርዓት ነው፡፡

3.3 "የውጭ ባለሙያ" ማለት በተወሰነ የኤክስፖርት ተኮር የሥራ ዘርፍ ልዩ ክህሎትና እውቀት ያለው የውጭ አገር ዜጋ ወይም መኖሪያው ውጭ ሀገር የሆነ ኢትዮጵያዊ ነው፡፡

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ለሚያስፈልጋቸው ልዩ የሙያ ድጋፍ የሚቀጥሩዋቸው የውጭ ባለሙያዎች በወጪ መጋራት ሥርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ጥያቄ በሚያቀርቡ ባለሀብቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

5. <u>ዓላማ</u>

በኤክስፖርት ተኮር የሥራ ዘርፍ የተሰማሩ/የሚሠማሩ ባለሀብቶች ያሰባቸውን የሙያ፣ የሥራ አመራርና አጠቃላይ የማኔጅመንት ችግር ለማሻሻል ከውጭ የተለያየ የክህሎትና ሙያ ደረጃ ያላቸውን የውጭ ባለሙያዎችን ለተወሰነ ጊዜ በማስመጣት በሚያሠሩበት ወቅት ለባለሙያዎች የሚከፍሉትን ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም ከገቢ ግብር ነፃ በማድረግ የባለሀብቶችን ወጪ መንግስት እንዲጋራ ማድረግ ነው።

6. <u>በወጪ መጋራት ሥርዓት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ባለሀብቶች</u>

6.1 በወጪ መጋራት ሥርዓት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ባለሀብቶች በሚከተሉት የሥራ መስኮች ላይ ተሰማርተው የሚገኙ መሆን ይኖርባቸዋል።

ሀ/ በማምረት እና/ወይም በማቀነባበር ምርታቸውን ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሪ በማፍራት ላይ ያሉ/ሊያፈሩ የሚችሉ እንደ ጨርቃጨርቅና አልባሳት፣ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች፣ አግሮ ፕሮሰሲንግ፣ ብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ፣ ኤሌክትሮኒክስ፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ ሥጋ፣ የሥጋ ውጤቶች፣ ዓሣ፣ ዕደ-ጥበብና የመሳሰሉት፣

ለ/ የሀገር ውስጥ እምቅ ሀብትን በመጠቀም ተጨማሪ እሴትን በመፍጠር በዚህ አንቀጽ ንዑስ ተራ ፊደል "ሀ" ለተመለከቱት ባለሀብቶች እንደ ማሽነሪ፣ አክሰሰሪና ኮምፖነንት፣ በከፊል የተጠናቀቁ ምርቶችና የመሳሰሉትን ግብዓቶች የሚያቀርቡ ስለዚህም ቀጥተኛ ባልሆነ ባሊንት የግብዓት ቅብብሎሽ ውል የሚያቀርቡ፣

6.2 የወጪ መጋራት ሥርዓት በፕሮጀክት ደረጃ ላይ ያሉና ማምረት ሲጀምሩ ምርቶቻቸውን ኤክስፖርት የሚያደርጉ በግንባታ ወቅት የተለያዩ የሲቪል፣ የመካኒካልና የኤሌክትሪካል ምህንድስና ሥራዎች የምክር አገልግሎት ለማግኘት የውጭ ባለሙያ ለሚቀጥሩ ባለሀብቶች ጭምር ተፈፃሚ ይሆናል።

7. <u>በወጪ መጋራት ሥርዓቱ ተጠቃሚ ለመሆን ማሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች</u>

በወጪ መጋራት ሥርዓት ለመጠቀም ጥያቄ የሚያቀርቡ ባለሀብቶች ከማመልከቻቸው ጋር ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሰነድ ማስረጃዎች ማቅረብ ይኖርባታል።

### 7.1 የንግድ ሥራ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ

አግባብ ካለው የመንግሥት አካል የተሰጠ አዲስ ወይም የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ።

### 7.2. የፕሮጀክት መግለጫ

አመልካቹ የድርጅቱን አጠቃላይ ሁኔታ ሲያመለክት የሚችል ቢያንስ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚያዘጋጀውና ከዚህ በታች የተካተቱትን ነጥቦች በያዘ መልኩ የፕሮጀክት መግለጫ አዘጋጅቶ ማቅረብ ይኖርበታል።

ሀ/ ድርጅቱ የተሰማራበት የሥራ ዘርፍ፣

ለ/ የድርጅቱ ራዕይና የተልዕኮ መግለጫ፣

ሐ/ የድርጅቱ ዓመታዊ የማምረት አቅም፣ ዓይነትና መጠን/በብዛትና በወቅቱ በሚኖር የማምረቻ ዋጋ/፣

መ/ የድርጅቱ ዓመታዊ የኤክስፖርት ምርት ዓይነትና መጠን/በብዛትና በወቅቱ በሚኖር የማምረቻ ዋጋ/፣

ሠ/ ድርጅቱ የፈጠረው ወይም ሊፈጥር የሚችለው የሥራ ዕድል በሙያ ዓይነት፣

ረ/ የድርጅቱ ካፒታል በዓይነት፣ በብዛት በዋጋ፣

ሰ/ ድርጅቱ ባለፉት ሁለት ዓመታት በኤክስፖርት ገበያ ላይ ተሰማርቶ የነበረ ከሆነ ሲያደርግ የነበረውን የኤክስፖርት ሽያጭ አፈጻጸም እና መረጃዎች፣

ሸ/ ድርጅቱ ግንባታ ላይ ከሆነ ወደ ሥራ የሚገባበት ጊዜ፣

ቀ/ በቅርበት የሙያ ድጋፍ ከሚያደርግለት የመንግስት ተቋም የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ።

### 7.3. የባለሙያው የሥራ መግለጫ

ሀ/ በወጪ መጋራት ሥርዓት ለመጠቀም የውጭ ባለሙያው ያስፈለገበትን ዝርዝር ምክንያት፣ባለሙያው ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይና በኮንትራቱ ዘመን መጨረሻም ለድርጅቱ የሚያበረክተውን ውጤት ለማሳየት ባለሙያው የሚያከናውናቸውን ዝርዝር የሥራ ተግባራት እና ከውጭ ባለሙያው ጋር የሚሠሩ ኢትዮጵያዊያን ባለሙያዎችን እንደሚያበቃ የሚያመለክት የስራ ዝርዝር መመሪያ ተዘጋጅቶ በአመልካቹ ፊርማ ተረጋግጦ መቅረብ ይኖርበታል።

ለ/ ከውጭ የሚመጣው ባለሙያ በቀረበው የፕሮጀክት ፕሮፖዛል መሠረት የተመለከተውን የሥራ ዝርዝር የማከናወን ብቃት ያለው ስለመሆኑ የሚያመለክቱ የትምህርቱን፣ ያለፉ የሥራ ተሞክሮዎቹን፣ እና ሌሎች መረጃዎችን እንዲሁም ሥራውን ለማከናወን የጠየቀውን የክፍያ መጠን ማቅረብ ይኖርበታል።

ሐ/ ሥራውን ለማከናወን የሚቀጠሩት የውጭ ባለሙያዎች በኮንትራት ጊዜ ገደብ ውስጥ አመልካቹ ባቀረበው የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ላይ የተመለከቱትን ውጤቶች የሚያስገኙ መሆኑንና ይህንንም እውን ለማድረግ የሚያከናውኗቸውን ዝርዝር ተግባራት በጊዜ ሰሌዳ በማሳየት እንዲሁም ዝርዝር ተግባራቱን ለማከናወን የሚከተሉትን ስልት/ስትራቴጂ/ በዝርዝር በማመልከት ማቅረብ ይኖርበታል።

መ/ የውጭ ባለሙያው ወይም የባለሙያው አስተዳዳሪ ድርጅት በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ለ" በቀረበው የድርጊት መርሀ-ግብር መሠረት ሥራውን የሚያከናውን ስለመሆኑና ስለክፍያውም አፈጻጸም ሁኔታ የኮንትራት ውል ስምምነት ከአመልካቹ ጋር መፈረም ይኖርበታል። የኮንትራት ስምምነቱም ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መቅረብ አለበት።

## 7.4. <u>የስራ ፍቃድ</u>

ከውጭ የሚቀጠሩ ባለሙያዎች የሚሰሩት ስራ በሀገር ውስጥ ባሉ ባለሙያዎች በብቃት ሊተገበር የማይችል መሆኑ ታምኖበት በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠ የሥራ ፈቃድ ማቅረብ ይኖርበታል።

## 8. <u>የወጪ መጋራት ሥርዓት የተጠቃሚነት ፈቃድ</u>

8.1 በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ሥር የተደነገጉት ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በወጪ መጋራት ሥርዓት ተጠቃሚ የሚሆነው ባለሀብት ከውጭ የሚያስመጣቸው ባለሙያዎች የድርጅቱን አቅም ከፍ ለማድረግ የሚችሉ ከፍተኛ የሥራ አመራር ክህሎትና የቴክኒክ እውቀት ያላቸው መሆኑን እንዲሁም ባለሙያዎቹ የሚያከናውኑት ሥራ አገር ውስጥ ባሉ ባለሙያዎች በብቃት ሊተገበር የማይችል መሆኑን በባለሀብቱ የቀረበውን ማስረጃ በመመርመር ሲያረጋግጥ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ባለሀብቱ የወጪ መጋራት ሥርዓቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ይፈቅዳል።

8.2. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለባለሀብቱ የሚያስፈልጉትን የውጭ ባለሙያዎች ቁጥር ባለሀብቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7.2 መሰረት ያቀረበውን ፕሮጀክት መግለጫ መሰረት በማድረግ ይወስናል።

8.3. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ባለሀብቱ በወጪ መጋራት ሥርዓት ተጠቃሚ እንዲሆን ከወሰነ ውሣኔው እንዲታወቅና ለክትትል እንዲያመች ለተጠቃሚው፣ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር፣ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እና ለሚመለከተው ተቋም ያሳውቃል፡፡

## 9. የወጪ መጋራት ሥርዓት ተጠቃሚዎች ግዴታ

በወጪ መጋራት ሥርዓት የውጭ ባለሙያ የሚቀጥር ማንኛውም ባለሀብት ከባለሙያው ጋር በሚያደርገው ውል መሠረት ባለሙያው ክህሎቱን ሥልጠና ለኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች እንዲሰጥ በማድረግ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10.4 መሠረት በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች እንዲተካ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡ ባለሀብቱ ይህን ካላደረገ በወጪ መጋራት ስርዓቱ ቀሪ የተደረገውን ታክስ እንደሚከፍል ግዴታ ይገባል፡፡

## 10. የገቢ ግብር ነፃ ዕድል የሚቆይበት ጊዜ

10.1 በኤክስፖርት ተኮር የሥራ ዘርፍ የተሰማራ ባለሀብት ከውጭ አገር ቀጥሮ ለሚያስመጣቸው ባለሙያዎች የፕሮጀክት ጊዜን ጨምሮ ከገቢ ግብር ነፃ የመሆኛ ጊዜ የሚቆየው፡

ሀ/ ምርቶቻቸውን ሙሉ በሙሉ ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡ ባለሀብቶች እስከ አምስት ዓመት፣

ለ/ ከምርታቸው 50% እና ከዚያ በላይ ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡ ባለሀብቶች እስከ 3 ዓመት

ሐ/ ከምርታቸው 20% በመቶ የማያንሰውን እና ከ50% በታች ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡ ባለሀብቶች እስከ 2 ዓመት ሆኖ በሁለተኛው ዓመት መጨረሻ ከምርታቸው 50% እና ከዚያ በላይ ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ ከሆነ አንድ ዓመት ይራዘምላቸዋል፡፡

10.2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (10.1) የኤክስፖርት መጠኑን በማሳደግ ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡ ባለሀብቶች የተፈቀደው የገቢ ግብር ነፃ መብት መጠቀሚያ የጊዜ ገደብ ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡ ባለሀብቶች ግብዓት ለሚያቀርቡ ባለሀብቶችም በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

10.3 በኤክስፖርት ተኮር የሥራ ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች የኤክስፖርት ምርት ለማምረት ለተጨማሪ የማስፋፊያ ፕሮጀክት እስከ ሁለት ዓመት ይሆናል።

10.4 የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በባለሀብቱ ጥያቄ ሲቀርብለት በሥሩ ከሚገኙ ተቋማት እና/ወይም ከሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን መረጃ በማሰባሰብ እያንዳንዱ የውጭ ባለሙያ ለኢትዮጵያዊ ባለሙያ የእውቀት ሽግግር ለማድረግ የሚያስፈልገውን የጊዜ ርዝመት በመወሰን በዚህ አንቀጽ ከ10.1 እስከ 10.3 የተጠቀሰውን የገቢ ግብር ነፃ መብት መጠቀሚያ የጊዜ ገደብ ሳያልፍ በወጪ መጋራት ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን ጥያቄ ላቀረበው ባለሀብት ፈቃድ ይሰጣል።

10.5. ባለሀብቱ በወጪ መጋራት ሥርዓት ተጠቃሚ የሚሆንበት የጊዜ ገደብ የሚጀምረው የወጪ መጋራት ሥርዓት የተጠቃሚነት ፈቃድ ለባለሀብቱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

10.6. ባለሀብቱ ለአንድ የውጭ ባለሙያ በተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ውስጥ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርን እያስፈቀደ ሌላ የውጭ ባለሙያን በመተካት በሥርዓቱ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

11. <u>የግምገማና ክትትል ሥርዓት</u>

11.1 ባለሀብቱ ስለባለሙያው የሥራ አፈጻጸም እና ባለሙያው እውቀቱን እና ክህሎቱን በማስተላለፍ የድርጅቱን ሥራ አፈፃፀም በማሻሻል ረገድ ስላመጣው ለውጥ በየስድስት ወሩ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሪፖርት ያቀርባል።

11.2 የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከውጭ ባለሙያው ጋር የተደረገውን የኮንትራት ውል ስምምነት መሠረት በማድረግ አስፈላጊውን የቅርብ ክትትልና ግምገማ በየስድስት ወሩ ያካሂዳል። ይህም ግምገማ ከሌሎች መካከል የውጭ ባለሙያው ያለውን ክህሎት እና እውቀት ለኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ያስተላለፈ መሆኑን ማረጋገጥ የሚያስችል መለኪያ ሊኖረው ይገባል።

11.3 የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 11.2 መሰረት በሚያደርገው የክትትልና ግምገማ ስራ የውጭ ባለሙያው ያለውን ክህሎት እና እውቀት ለኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች በቂ በሚባል ደረጃ ያላማስተላለፉን ያረጋገጠ እንደሆን ለባለሀብቱ የተሰጠውን የወጪ መጋራት ፈቃድ መሰረዝ አለበት።

11.4 የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በወጪ መጋራት ስርዓቱ ተጠቃሚ የሆኑ ድርጅቶችን ዝርዝር፣ የተሰጠውን የወጪ መጋራት የድጋፍ መጠን.....ወዘተ የያዘ አጠቃላይ የወጪ መጋራት የአፈፃፀም ሪፖርት የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ (እስከ መስከረም 30) ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እና ለኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ማቅረብ አለበት።

## 12. የሥልጣን ውክልና

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ይህን መመሪያ ለማስፈፀም በወጪ መጋራት ሥርዓት ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸውን በኤክስፖርት ተኮር የሥራ ዘርፍ የተሰማሩትን ባለሀብቶች በመገምገም የዕድሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንዲወስንና ይሆኑ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴርና ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እንዲያስተላልፍ የሥልጣን ውክልና ተሰጥቶታል።

## 13. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ይህን መመሪያ በሥራ ላይ በሚውልበት ዕለት በተሻረው መመሪያ የተፈቀደላቸውን የወጪ መጋራት ሥርዓት የጊዜ ገደብ ተጠቅመው ያልጨረሱ ባለሀብቶች በዚህ መመሪያ በተፈቀደው ተጨማሪ የጊዜ ገደብ ለመጠቀም የሚያቀርቡትን ጥያቄ በመገምገም በተጨማሪው የጊዜ ገደብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሊፈቅድ ይችላል።

## 14. የተሻረ መመሪያ

በኤክስፖርት ተኮር ዘርፍ ተቋማት ውስጥ ያለውን የሥራ አመራር ለማሻሻል የሚቀጠሩ የውጭ አገር ባለሙያዎች ከገቢ ግብር ነፃ ለማድረግ የወጣው መመሪያ ተሽሮ በዚህ መመሪያ ተተክቷል።

## 15. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከየካቲት 24 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት 20 ቀን 2010 ዓ.ም

አብርሃም ተከስተ (ዶ/ር)
የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስትር